# ተው ምረር ተው ምረር

እውነት ወህኒ ወርዳ ፣ ተፈትቶ ግፈኛ
ታማኝ አቀርቅሮ ፣ ገኖ ከዳተኛ
ደካሞች ሰልጥነው ፣ ተዳክሞ ሃይለኛ
ባገር ላይ ተጭኖ ፣ ባንዳ ከዳተኛ
አህያም ፈነጨች ፣ አንበሳው ቢተኛ ።

በግፍ ተፈናቅሎ ፣ ከቀዬው ተሳዶ
አቃጥሎ ሲፈጀው ፣ ሲያደርገው ማገዶ
ባንካሴ ገጀራ ፣ እየጣለው አርዶ
ባራቱም ማዕዘን ፣ ስቃይ ስሩን ሰዶ
እንዴት ሰው ይኖራል ፣ መከራን ተላምዶ ።

ምን ያለ ግፈኛ ፣ ምን ትውልድ በቀለ
እኮ ምን ባጠፋ ፣ እኮ ምን በደለ
አንከፋፈልም ፣ አንድነሁን ባለ
ያገሩን አደራ ፣ በጫንቃው ባዘለ
አትበታተንም ፣ ኢትዮጵያ ስላለ
ላገሩ በሞተ ፣ ላገር በቆሰለ
ውለታው ተረስቶ ፣ አይከፍሉ ከፈለ ።

ትዕግስትም ልክ አለው ፣ ማብቂያ መዳረሻ
ባንዶች አሳድገው ፣ ጃስ ያሉትን ውሻ
ታሪኩን ለማያውቅ ፣ ትምህርትን ለሚሻ
ይሄን ዘረ ድርቡሽ ፣ አሳጣው መድረሻ
ምንሽር ጓንዴህን ፣ አርገው መፈተሻ
እናቱ ማህፀን ፣ ሲያሻው ይግባ ዋሻ ።

ተው ምረር ተው ምረር ፣ ምረር እንደ ቅል
አልመርም ብሎ ነው ፣ ዱባ እሚቀቀል
    በደልና ግፉን ፣ ይብቃህ አትላመድ
    ጠላት ጠላት እንጂ ፣ አይሆንህም ዘመድ
የሚለውን ብሂል ፣ ፈክርና ውጣ
እስኪ እንዳራስ ነብር ፣ ጨክነህ ተቆጣ
    ተው ምረር ተው ምረር ፣ ምረር እንድ ኮሶ
    አሳዳጅ ተሳዶ ፣ ይለምን አልቅሶ
    የማን ቤት ይለማል ፣ የማን ጎጆ ፈርሶ ።

ታዛቢው

May 12, 2018